ያማል
እና እንደነገርኩሽ የሚወዱትን ሰው ቀጥረው እንደመጠበቅ
የነፍሰጡርን ሞት አይቶ እንደመሳቀቅ
ባልታሰበ ናዳ ተመቶ እንደመድቀቅ
ከተስፋ ጉልላት ተገፍቶ እንደመውደቅ
ተአምር በበዛባት በዚች ቧልተኛ አለም
ከዚህ የበለጠ ምንም ህመም የለም
አውቶቡሱ ያማል
ሚኒባሱ ያማል
ላዳ ታክሲው ያማል
የማይጎል የሰው ጎርፍ ደራሽ ማዕበሉ
የእንባ ቅጥልጥሉ ምን ብዬ ልንገርሽ ያማል ይሄ ሁሉ
እና እንደነገርኩሽ የሚወዱትን ሰው ቀጥረው ካረፈደ
የሚያፈቅሩትን ሰው ቀጥረው ካረፈደ
ነገር ተበላሸ ህመም ተወለደ ጨጉራ በገነ
እሳት በእንፋሎት መልክ በእኸታ ተነነ
የሚሆነው ሳይሆን የማይሆነው ሆነ
ሁሉ ተቀይሮ ተተካ በሲቃ
ምን ብዬ ልንገርሽ ይሄም ያማል በቃ
ወጪ ተራማጁ አስመሳይ ሰጋጁ
ፀሀዩ ዝናቡ
የ ለምን ምክንያት የ ለምን ሰበቡ
ተቆራጭ አበባ ሊቆረጥ ማበቡ
ውል የለሽ ደመና ተራራ መክበቡ
እልፍ አእላፍ ኮከብ ጨረቃን ማጀቡ
ደግሞ ለርሷ ግጥም እናትዋን ጨረቃ
ምን ብዬ ልንገርሽ ይህም ያማል በቃ
እና እንደነገርኩሽ ጉንጭ የማትሞላ ኬክ አስር ብር የሸጠ
የካፌ አሳላፊ ወደ እኔ አፈጠጠ
ዘይት የነካውን መንታ እጁን አጣምሮ
ምን ልታዘዝ ይላል ቁልቁል አቀርቅሮ
ምን ልታዘዝ? ይላል
እንዴት ቅጥሉ ሰው ቅጥሉን ሰው ያዛል
ማኪያቶ ልዘዝ?
ካፑቺኖ ልዘዝ?
ጥቁር ቡና ልዘዝ?
ለምን ሰው አላዝም?
መታዘዝ መናዘዝ እርግማን የሆነውም
ካፌውን ሲያሳልፍ
እራሱ ግን የሚያልፍ
ቁልቁል አቀርቅሮ
ሞቱን በአንገቱ ቀብሮ
ምን ልታዘዝ? ይላል
አንድ ማኪያቶ ከአንድ እሷ ጋር ልበል?
አንድ ካፑቺኖ ከአንድ እሷ ጋር ልበል?
ከጥቁር ቡና ጋር እሷን አምጣ ልበል?
ተይ አታስለፍልፊኝ ይህ ሁሉ ያማል
የላስቲክ አበባ የአርቲቡርቲ ስዕል
የጭቃ እሾህ ወግቶት እኹ ያወጣ ቁስል
ትልቁ ነቀዝ ሰው የማንቀዙን ያህል
ብዙ አታስለፍልፊኝ ይህ ሁሉ ያማል
እና እንደነገርኩሽ ላንቺ የያዝኩት አበባ መጠውለግ አመጣ

ፀሀይ ገባ ወጣ
ዝናብ ቀረት መጣ
ጨረቃ የለችም እናትዋን ስላልኳት?
ደግሜ ሰድቤ ሺህ ዓመት እንዳይገርማት
እናትዋን እናትዋን ጨረቃ
ተይ አታስለፍልፊኝ ይህም ያማል በቃ
ግን እኔ አንቺን ስወድሽ
እኔ አንቺን ስወድሽ
ይህን ሁሉ ችዬ ነው የምጠብቅሽ
ቢሆንም ግን ያማል!

ሰለሞን ሳህሌ